# ጠንቀቅ እንበል

መስፍን ወልደ ማርያም

ሐምሌ 1995



የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስለድንበር ጉዳይ ዘርዘር አድርገው ሲናገሩ እንደባለሙያ እንጂ እንደሚኒስትር አልነበረም፤ ሙያው ደግሞ እንደሌላቸው የተናገሩት ሁሉ ያመለክታል። በመጀመሪያ ድንበር መካለልን 'እርግማን' ያሉት ለምን እንደሆነ አልገባኝም፤ ከቅኝ ገዢ ኃይሎች ጋር አፄ ምኒልክ መዋሰናቸው እርግማን አይደለም፤ በኢትዮጵያ ታሪክ የድንበር መካለል ግዴታ ያጋጠመን በአፄ ምኒልክ ዘመን ከአድዋ ጦርነት በኋላ ነበር። እስከዚያን ጊዜ ድንበር መካለሉ አለማስፈለጉ ኢትዮጵያን የሚያኮራት ታሪክ ነው፤ ብቸኛ ሀገረ መንግሥት እንደነበረች የሚያሳይ ማስረጃ ነው። ድንበር መካለል የኢትዮጵያ ወይም የአፍሪካ እርግማን ሳይሆን የዓለም አገሮች በሙሉ፣ ትልቅ ትንሽ ሳይል የኃይል ሚዛንን ጠብቀው የፈጸሙት ስምምነት ነው። ያንን ድንበር አስከብሮ ማቆየት የተከታታይ ትውልድ ግዴታ ነው፤ ግዴታው ከተሰማቸው። እርግማን የሚሆነው በደም፣ በታሪክና በባህል የተቆራኘውን ሕዝብ ማስገንጠሉና ባዕድ ማድረጉ ነው፤ ይህ ያለጥርጥር የአባቶችን የውርስ ቃል ኪዳን ማፍረስ ነውና እርግማን ሊባል ይቻላል፤ ድንበር ማከለል ግን እርግማን አይደለም።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዝርዝር መግለጫ መሠረት በደንብ የተከለሉትን የኢትዮጵያ ድንበሮች ሲገልጹ የቀድሞው የብሪታንያ ሶማሊላንድን ድንበር አላነሡም፤ ይህ ድንበር በዓለም ውስጥ በደንብ ተከልለዋል ከሚባሉት ድንበሮች አንዱ ነው፤ አብዛኛውን ሄጀበታለሁና አውቀዋለሁ። ችግሩ ያለው በኢትዮጵያና በቀድሞው የኢጣልያ ሶማልያ መሀከል ያለው ድንበር ላይ ነው። በኢትዮጵያና በኬንያ መሀከል ያለው ድንበር በቢሮክራቶች ሲከለል ወደመጨረሻው ላይ የጉዳዩ ኃላፊ የነበሩት ጄኔራል



WWW.MESFINWOLDEMARIAM.ORG

ቢሮዬ መጥተው አሳዩኝ፤ የኢትዮጵያ፣ የኬንያና የሱዳን ሦስትዮሽ መጋጠሚያ ላይ ያለው ነጥብ በሦስቱም ካልተወሰነ ችግር ሊያመጣ ስለሚችል በእንጥልጥል እንዲቆይ የሚል አስተያየት ሰጥቻቸው ስምምነቱ ውስጥ የገባ ይመስለኛል።

ከሱዳን ጋር ስላለውም ድንበር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ የዘለሉትና በመዝለላቸውም ከባድመና ከኢሮብ የባሰ አደጋን የሚያስከትል የሚመስለኝ ነገር አለ። ከዚህ በፊት በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የኢትዮጵያን የሱዳንን ድንበር የሚያጠና የቢሮክራቶች ኮሚቴ ተቋቁሞ፣ ጥናቱም ለመንግሥት ቀርቦ፣ በዚያው መሠረት ድንበሩ እንዲስተካከል ውሳኔ ከተደረሰ በኋላ በጊዜው በነበረው ምክር ቤት (ከዛሬው በጣም የተለየ ነበር፤) ትልቅ ረብሻ አስነሣና ሳይፈጸም ቀረ። በደርግ ዘመን ደግሞ የሱዳን ድንበር ጉዳይ እንደገና ተነሥቶ ነበር፤ በእኔ ሰብሳቢነት በተለያዩ መስኮች ባለሙያ የሆኑ የዩኒቨርሲቲ መምህራን በአንድነት ለብዙ ጊዜ እንድናጠናው ተደረገ፤ ከነዚህም ውስጥ ዶር. ብርሃኑ አበበ፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት፣ ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደ አረጋይ በሕይወት አሉ፤ ውጤቱ ስድስት ወይም ሰባት ጥራዝ ጽሑፍና ማስረጃ ነበር። ትልቁ ነገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከጠቀሱት የጉዊን መስመር ከሚባለው ውጭ ሌላ በደብዳቤ ልውውጥ የተደረገ የሱዳንን ድንበር ማስተካከያ እንደነበረ የቢሮክራሲው የጥናት ኮሚቴ ሳይደርስበት መቅረቱና የዩኒቨርሲቲው ኮሚቴ ይህንን አዲስና ጠቃሚ መረጃ ማግኘቱ ነበር። ከአነጋገራቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩም የደረሱበት አይመስልም። እነሱ የምትለውን የቢሮክራሲው ኮሚቴ ጥናት ብቻ እንብበው ከሆነ አገሪቱ ችግር አላት።

በደብዳቤው ልውውጥ የተደረገው ስምምነት ከግዊን መስመር የሚወጣና ለኢትዮጵያ ጠቃሚ መሬት የሚሰጥ ነው። አሁን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲናገሩ



WWW.MESFINWOLDEMARIAM.ORG

እንደሰማኋቸው አንደኛ ከግዊን መስመር በቀር ሌላ ነገር አላነሡም፤ ሁለተኛ ከዚህ በፊት (በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ማለታቸው ይመስለኛል) መንግሥት ተስማምቶ ነበር ማለታቸው በተነሣው የውስጥ ተቃውሞ ምክንያት ጉዳዩ መሞቱንና በደርግ ጊዜ ሲያንሰራራ ሌላ ጥናት መደረጉንና ለኢትዮጵያ በሚጠቅመው አውነተኛ መልኩ መወሰኑን አልገለጹም።

የግዊን መስመር በስዕሉ ላይ እንደሚታየው ከጋላባት ወደኦም ሀገር የሚሄድ ነበር፤ ግን በደብዳቤ ልውውጥ መስመሩ ተለውጦ በመስመሮቹ መሀከል ያለው መሬት የኢትዮጵያ ሆኗል፤ ይህ መሬት የጉዋንግንና የአንገርብን ወንዞች አቋርጦ ተከዜ ወንዝ ላይ የሚደርስ በመሆኑ ደለል መሬት የያዘ ስለሆነ በጣም ለም ነው።




ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ መግለጫ በኋላ ሌላ አስደንጋጭ ወሬ ተሰማ፤ አልሳሃፋ የሚባል የሱዳን ዕለታዊ ጋዜጣ እንደዘገበው አልቃሊባት በሚባል የሱዳን ከተማ የኢትዮጵያና የሱዳን ሚኒስትሮችና 'የአማራም ገዢ' ተሰብስበው በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ትእዛዝ



WWW.MESFINWOLDEMARIAM.ORG

300,000 (ሦስት መቶ ሺህ ሄክታር ወይም ሰባት ሺህ አምስት መቶ ጋሻ) ለም መሬት ለሱዳን እንዲሰጥ ተወስኗል ይላል። ይህ መሬት የኢትዮጵያ ገበሬዎች ከፍ ያለ የማሽላና የሰሊጥ ምርት የሚያገኙበት እንደነበረም ይናገራል። ወሬው ፍፁም ዉሸት መሆኑን ረፖርተር ጋዜጣ ስሙ ያልተገለጸ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣን ጠቅሶ የብዙ ሰዎችን ሥጋት አስወግዷል።

የዚህን ድንበር ጉዳይ ሱዳን ጊዜንና ዕድልን እየጠበቀች የምታነሳበት ምክንያት ግልፅ አይደለም፤ ስለዚህም ሕጋዊ መደምደሚያ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነው፤ በሱዳን በኩል ሲታይ ይህንን መሬት ለማግኘት ምናልባት የተመቸ ጊዜ ይመስል ይሆናል፤ በኢትዮጵያ በኩል ሲታይ ደግሞ ሁኔታው ጭራሽ የማይመች ነው፤ በኤርትራ በኩል የሆነው ሁሉ በስሕተትም ይሁን ሆን ተብሎ በተደረገ እቅድ የአገሪቱ ቁስል ሳይሽር ሌላ ቁስል በሱዳን በኩል የተጨመረ እንደሆነ ከባድ አደጋን የሚያስከትል ይሆናል። የሱዳንን ግዜያዊ ወዳጅነት ለማግኘት ኢትዮጵያ እጅ መንሻ የምታቀርብበት ምክንያት የለም።